# የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን)

The Ethiopian Medhin Democratic Party (MEDHIN)

የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ ሙሉ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎቹ በተገኙበት፣ በሊቀመንብሩ ፕሮፌሰር ሥዩም ገላዬ እየተመራ፣ መደበኛ ስብሰባውን፣ በጁላይ 31 እና በኦገስት 1፣ 2010 ዓ.እ. በታላቅ ሥርአት አጠናቆ ለአባሎቹና ለደጋፊዎቹ የሚከተለውን ጥብቅ መመሪያና ከፍተኛ ውሳኔዎችን በጠቅላላ ድምፅ አሳልፏል።

በመጀመሪያም፣ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር ተደርጎባቸው ለኢትዮጵያውን ወገኖቻችን በሙሉ፣ በመድኅን ድሕረ-ገፅ በሠፊው እንዲዳረስና እንዲታወቅ ታስቦ ወያኔን ለማጋለጥ የተሰራጩትን የታሪክ ምርምርና የጥናት ውጤቶች በሙሉ በመዳሰስ፣ ታላቅ አድንቆቱን መዝግቧል። የተከበራችሁ አንባቢዎቻችንን፣ ድጋፍ፣ ትብብርና አስተዋፅዖም በአክብሮት ይጋብዛል። የድሕረ-ገፁ URL<www.medhin.org> ነው።

ቀጥሎም፣ ጎሰኛ አሸባሪና አምባገነንናዊ የሆነውን፣ ወያኔ «አቢዮታዊ ዲሞክራሲ » እያለ ስለሚመጻደቅበት ርእዮት የተደረገውን ዝርዝር ጥናት ተመልክቷል። ጥናቱ፣ በዚህ የተንኮል ሥርአት ሥር የተዘረጋውን ጠባብ የኮሙኒስት የጭቆና መርህና የበቀለኛ የአስተዳደር ቅድመ ዝግጅት የሚያወግዘው በጠለቀ ምርምር ላይ ተመርኩዞ በመሆኑ፣ የፓርቲውን ከፍተኛ አድናቆት አትርፏል። (የወያኔን 1985 ዓ.እ. የከይሲ ግብ ያጢኑት።)

እንዲሁም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ የሕዝቡን አንድነት እና የተፈጥሮና የዜግነቱን መብቶች በሙሉ፣ ደደቢት ላይ ባረቀቁት «ሕገመንግሥታዊ» ተንኮል  ከልሰውታል። ወያኔዎች፣ ጠባብ ብሄረተኝነትን እና ጎሰኝነትን፣ ተገን አድርገው፣ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር መሸርሸሩን፣ የሕዝቡን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ትሥሥር ማናጋቱን፣ የቆየ ታሪኩና እድገቱ ደብዛቸው እንዲጠፋ መሥራቱን የሕይወታቸው ተልእኮ ካደረጉት ውሎ አደረ።

«ከድጡ ወደ ማጡ» እንዲሉ፣ ወያኔ ይሉኝታ ባጣ ሙሰኝነትና ወገናዊነት፣ ገበሬውን ከርስቱና ከቤቱ ነቅሎ፣ ምርጥ መሬቱንና የውሃ ተፋሰሶችን፣ በምስጢር ለባእዳን ልማትና ጥቅም  ማኮናተሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። ኮንትራቱ ለብዙ ዓመታት፣ ቁጥጥር አልባ በሆነ ውል  የታሰረ በመሆኑ፣ «በሃገር ከሃዲነት» የኢትዮጵያዊያንን እና የመጭውን ትውልድ ሐብትና ንብረት በመሸጥ የተፈፀመ «እጅግ ከባድ ወንጀል» ነው።  ስለሆነም፣ በኢትዮጵያና በትውልዷ ላይ ምን ጊዜም የማይፀና ውል መሆኑን የመድኅን ፓርቲ በጥብቅ ያሳውቃል። ይህንንም ይቅርታ የማይገኝልት የወያኔ ክህደት በስብሰባው  አውግዟል፤ ኰንኗልም።

በጎጠኝነትና በዘረኝነት መላውን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ለመበከል፣ የኑሮው እድገትና የደሕንነቱ መተማመኛ የሆኑትን መሠረታዊ የመኖሪያ፣ የትምሕርት፣ የሥራና የኢኮኖሚ አውታሮቹን በተያዥነት ይጠቀምባቸዋል። ሕዝቡን፣ "ካለ ወያኔ በስተቀር የመረጥከ እንደሆን ወዮልህ አንተን አያርገኝ" እያለ በማስፈራራት፣  በ 99.6% ምርጫውን ማሸነፉን ነግሮናል። የወያኔ ሥርዓት ኢሰብአዊ፣ ኢፍትሐዊ ብሎም በምቀኝነትና በጭካኔ የተዘፈቀ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በዚህ ቅጡን ባጣና ውሸትና እብሪት ልዩ ምልክቱ በሆነ ሥርዓት ሥር ነው የሚገዛው። ይህንን ሽብርተኛ የሆነ አምባገነናዊ አናሳ ፓርቲ፣ ወንጀላዊ ሴራዎቹን፣ ለተገንጣይነት የሚያበቁትን ቅድመ ዝግጅቶቹንና ከይሲ ተግባሮቹን በሙሉ፣ አጋልጧል፤ በታጋሹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥምም፣ ፀረ ዴሞክራሲውን ወያኔ በታላቅ ድምፅ አውግዟል።

# ጥብቅ መመሪያና ከፍተኛ ውሳኔዎች

1ኛ ወያኔ አጥፊነቱን ደጋግሞ በገሃድ አረጋግጧል፤ ማስርጃዎቹም ብዙ ናቸው። በማንኛቸውም የሰላማዊም ሆነ የዲሞክራሲያዊ የነፃነት ትግል ሚዛን፣ ወያኔ ሽብርተኛ፣ አምባገነናዊ እና ጨቋኝ ነው። ፋሽሽታዊ አገዛዙን ለማንሰራፋት «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» እያለ የሚጠራውን ብቸኛና ጠባብ የኮሚኒስት ፓርቲ መርሆ ያራምዳል። ፋሺሽታዊና ጭፍን የሆነው የጎሰኛ ወራሪ ጠባዩ፣ እናት ኢትዮጵያን በጠላትነት ፈርጆ ያለይሉኝታ ህልውናዋን ለማፈራረስ ጠቅሞታል። የመላውን ኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅምና የጋራ እድገት የሚፃረረው «ሕገመንግሥት» እየተባለ የሚጠራው አዋጅ፣ አጥፊና ጠባብ ስለሆነ የወያኔን ጎሰኝነት ለማስፋፋት ካልሆነ በስተቀር አወንታዊ ፋይዳ የለውም፤ አይኖረውምም። ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳችም ውክልና ሳይኖረው የሃገሪቷን ለም መሬት፣ የባሕር በሮቿን፣ የማእድን ሃብቷንና ወንዞቿን በምስጢራዊ ሃራጅ መቸብቸቡን ተያይዞታል። ሕዝቡን ማስራቡና ማራቆቱ አንሶት በገሃድ በመረሸን አጥፊነቱን ወሰን የሌለው መሆኑን ደጋግሞ አረጋግጧል።

2ኛ በመጨረሻም፣ «ሕዝቡ 99.6% በሆነ ድምፅ መረጠኝ።» በማለት ሃፍረተ ቢስ የሆነ የዕብሪተኝነት ጠባዩን አሳየን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለራሱም ሆነ ለልጆቹ የፀነሰውን ዲሞክራሲያዊ የብዝህነተ ፓርቲ ስርአት ሽል አድርጎ አስቀረው፣ ተስፋውንም አዳፈነበት።

3ኛ ከመሠረቱ፣ የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓረቲ አቋም፣ መላውን የኢትየጵያ ሕዝብ ለተረጋገጠ ነፃነት፣ ፍትሕና እድገት የሚያበቁት የአንድነት የጋራ ትግል ስልት፣ ሁለገብ እንደሆነ ማመኑን፣ ዳግም እያስታወስን፣

4ኛ ኢትዮጵያዊያንን በሙሉ ያሳተፈና ያስተባበረ ሁለገብ የጋራ ትግል ብቻ ነው የወያኔን አምባገነናዊ፣ ጎሰኛና ሽብርተኛ ከይሲ ሥርዓት ለማንበርከክና ጨርሶ ለማጥፋት የሚችለው። ይህንን ዓላማ በቁርጠኝነት መከተል አማራጭ የሌለው ብቸኛ ብሄራዊ ግዳጃችን መሆኑን እያረጋገጥን፣

5ኛ ተስፋ ሳትቆርጡ፣ በከፍተኛ ጥረት ለሃገራችን ኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት፣ ነፃነትና ፍፁም የበላይነት የምትዋደቁ፣ በሃገር ቤትና በመላው ዓለም ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ሕይወታችሁን ያተረፋችሁት የኢትዮጵያ አርበኞች፣ ዲሞክራሲያዊ ተቃዋሚ የፖለቲካና የሲቪክ አጋር ድርጅቶች፣ በተለይም፣ ውድ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን በሙሉ፣ ባላችሁበት ሁለገብ የትግል ተሳትፏችሁ እንዳይጓደልና እንዳይቀዘቅዝ በእናት ኢትዮጵያ ስም አደራ እንላለን።

6ኛ የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች፣ ከዚህ በለይ የተመለከተውን ውሳኔ ድምቀት ባለው ሁኔታ አፅድቀው፣ የወቅቱን የጥናትና የምርምር አጀንዳዎችና ህቡዕ መመሪያዎችን ተለዋውጠዋል። የሥራ አስኪያጁ ኮሚቴ ከሁለት ወር በሃላ ለመገናኘት ተስማምቶ ስብሰባው ተበትኗል።

የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ።